የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ — የካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 19
ADDIS ABABA – 22nd February, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የወጣ
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፻፷፬

## CONTENTS

Proclamation No. 31/1996
Offences Against the Safety of Aviation
Proclamation ............................................... Page 164

### አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፹፰
### በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የወጣ አዋጅ

በበረራ ደህንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አስጊና የሰው ሕይወትና ንብረት በከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥሉ መሆናቸውን በመገንዘብ እንነዚህኑ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ለመቋቋም ዓለምአቀፍ ስምምነቶች የወጡና ኢትዮጵያ ስምምነቶቹን ከፈረሙ አገሮች አንዷ በመሆኗ፤

ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን ዓለምአቀፍ ስምምነቶች ወደ ተግባር ለመተርጎም የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አካል የሆነ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩· "በበረራ ላይ ያለ አይሮፕላን" ማለት የአይሮፕላኑ የውጭ በሮች ከተዘጉበት ጊዜ ጀምሮ በሩ እስከሚከፈት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ሲሆን አይሮፕላኑ ተገዶ ያረፈ እንደሆነ ይህ ጊዜ አይሮፕላኑንና በውስጡ ያሉትን ሰዎችና ንብረቱን ሙሉ በሙሉ ለማስለቀቅ የሚወስደውን ጊዜ ይጨምራል፤

### PROCLAMATION NO. 31/1996
### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR OFFENCES AGAINST THE SAFETY OF AVIATION

WHEREAS, realizing that offences against the safety of aviation greatly endanger life and property, international conventions of which Ethiopia is one of the signatory states have been adopted to suppress such offences;

WHEREAS, in order to implement the conventions ratified by Ethiopia, it is necessary to promulgate a law forming an integral part of the Penal Code;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short title*

   This Proclamation may be cited as the "Offences Against the Safety of Aviation Proclamation No. 31/1996."

2. *Definitions*

   In this Proclamation:

   1) "an aircraft in flight" refers to the period from the moment when all the external doors of an aircraft are closed following embarkation until the moment when any such door is opened for disembarkation; and includes, in case of forced landing, the time until the aircraft as well as the persons and property on board are released;

፪· "በአገልግሎት ላይ ያለ አይሮፕላን " ማለት የአየር ትራንስፖርት ወይም የአይሮፕላን ሠራተኞች ለተወሰነ በረራ ከሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ጀምሮ አይሮፕላኑ ካረፈ በኋላ እስከ ፳፬ ሰዓት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ሲሆን፣ በማናቸውም ሁኔታ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በበረራ ላይ ያለ አይሮፕላን ከሚሸፍነው ጊዜ ያነሰ አይሆንም።

፫· አይሮፕላን ስለመጥለፍ

ማንም ሰው ሆን ብሎ ከሕግ ውጭ በኃይል ሥራ ፣ በዛቻ ወይም በሌላ በማንኛውም የማስፈራሪያ ዘዴ በአገልግሎት ላይ ያለ አይሮፕላንን የያዘ ወይም በቁጥጥር ሥር ያዋለ እንደሆነ ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፬· በበረራ ላይ ያለን አይሮፕላን አስጊ ሁኔታ ላይ ስለመጣል

፩· ማንም ሰው በቸልተኝነት በበረራ ላይ ባለ አይሮፕላን ውስጥ በሰው ላይ የኃይል ሥራ ከፈጸመና ድርጊቱ የአይሮፕላኑን ደህንነት አስጊ ሁኔታ ላይ የሚጥል የሆነ እንደሆነ ከ፭ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪· ማንም ሰው ሆን ብሎ በበረራ ላይ ባለ አይሮፕላን ውስጥ በሰው ላይ የኃይል ሥራ ከፈጸመና ድርጊቱ የአይሮፕላኑን ደህንነት አስጊ ሁኔታ ላይ የሚጥል የሆነ እንደሆነ ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፭· በአገልግሎት ላይ ባለ አይሮፕላን ላይ አደጋ ስለማድረስ

፩· ማንም ሰው በቸልተኝነት በአገልግሎት ላይ ያለን አይሮፕላን ያወደመ ፣ ለበረራ ብቁ እንዳይሆን ያደረገ ወይም የበረራ ላይ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከ፭ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል ።

፪· ማንም ሰው ሆን ብሎ በአገልግሎት ላይ ያለን አይሮፕላን ያወደመ ፣ ለበረራ ብቁ እንዳይሆን ያደረገ ወይም የበረራ ላይ ደህንነቱን ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፮· በአገልግሎት ላይ ባለ አይሮፕላን ውስጥ አደጋ የሚያደርስ መሣሪያ ወይም ዕቃ ስለማስቀመጥ

፩· ማንም ሰው በቸልተኝነት በአገልግሎት ላይ የሚገኝን አይሮፕላን ለማውደም ወይም ለበረራ ብቁ እንዳይሆን ወይም የበረራ ደህንነቱን ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል መሣሪያ ወይም ዕቃ በማናቸውም ዘዴ በአይሮፕላኑ ውስጥ ያስቀመጠ ወይም እንዲቀመጥ ያስደረገ የሆነ እንደሆነ ከ፭ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪· ማንም ሰው ሆን ብሎ በአገልግሎት ላይ የሚገኝን አይሮፕላን ለማውደም ወይም ለበረራ ብቁ እንዳይሆን ወይም የበረራ ደህንነቱን ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል መሣሪያ ወይም ዕቃ በማናቸውም ዘዴ በአይሮፕላኑ ውስጥ ያስቀመጠ ወይም እንዲቀመጥ ያስደረገ የሆነ እንደሆነ ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፯· ለበረራ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችን ወይም መሣሪያዎችን ስለማሰናከል

፩· ማንም ሰው በቸልተኝነት ለበረራ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችን ወይም መሣሪያዎችን ያወደመ ፣ ያበላሸ ወይም አሰራራቸውን ለማሰናከል ጣልቃ የገባ እንደሆነና ድርጊቱ በበረራ ላይ የሚገኝን አይሮፕላን ለአደጋ የሚያጋልጥ የሆነ እንደሆነ ከ፭ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

2) "an aircraft in service" refers to the period starting from the time of the preflight preparation of the aircraft by ground personnel or by the crew for a specific flight until twenty-four hours after any landing; but it shall not, in any event, be less than the entire period during which the aircraft is in flight as defined in sub-Article (1) of this Article.

3. *Unlawful Seizure or Control of an Aircraft*

Whosoever intentionally and unlawfully seizes or exercises cortrol of an aircraft in service by violence or threats thereof or by any other form of intimidation is punishable with rigorous imprisonment from fifteen to twenty-five years.

4. *Endangering an Aircraft in Flight*

1) Whosoever negligently performs an act of violence against a person on board an aircraft in flight, which act is likely to endanger the safety of that aircraft, is punishable with rigorous imprisonment from five to fifteen years.

2) Whosoever intentionally performs an act of violence against a person on board an aircaft in flight, which act is likely to endanger the safety of that aircraft, is punishable with rigorous imprisonment from fifteen to twenty-five years.

5. *Damage to an Aircraft in Service*

1) Whosoever negligently destroys an aircraft in service or causes damage which renders it incapable of flight or which is likely to endanger its safety in flight , is punishable with rigorous imprisonment from five to fifteen years.

2) Whosoever intentionally destroys an aircraft in service or causes damage which renders it incapable of flight or which is likely to endanger its safety in flight, is punishable with rigorous imprisonment from fifteen to twenty-five years.

6. *Placing a Device or Substance on an Aricraft in Service*

1) Whosoever negligently places or causes to be placed on an aircraft in service, by any means whatsoever, a device or substance which is likely to destroy that aircraft or to cause damage to it which renders it incapable of flight or to endanger its safety in flight, is punishable with rigorous imprisonment from five to fifteen years.

2) Whosoever intentionally places or causes to be placed on an aircraft in service, by any means whatsoever, a device or substance which is likely to destroy that aircraft or to cause damage to it which renders it incapable of flight or to endanger its safety in flight, is punishable with rigorous imprisonment from fifteen to twenty-five years.

7. *Damage to Air Navigation Facilities or Equipment*

1) Whosoever negligently destroys or damages air navigation facilities or equipment, or interferes with their operation, which act is likely to endanger the safety of an aircraft in flight, is punishable with rigorous imprisonment from five to fifteen years.

፪· ማንም ሰው ሆን ብሎ ለበረራ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችን ወይም መሣሪያዎችን ያወደመ፣ ያበላሸ ወይም አሰራራቸውን ለማሰናከል ጣልቃ የገባ እንደሆነና ድርጊቱ በበረራ ላይ የሚገኝን አይሮፕላን ለአደጋ የሚያጋልጥ የሆነ እንደሆነ ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፰· <u>የበረራ ደህንነትን ለአደጋ ስለሚያጋልጥ ሀሰተኛ መረጃ</u>

፩· ማንም ሰው በቸልተኝነት በበረራ ላይ የሚገኝን አይሮፕላን ለአደጋ የሚያጋልጥ ሀሰተኛ መረጃ ያስተላለፈ የሆነ እንደሆነ ከ፭ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል ።

፪· ማንም ሰው ሆን ብሎ በበረራ ላይ የሚገኝን አይሮፕላን ለአደጋ የሚያጋልጥ ሀሰተኛ መረጃ ያስተላለፈ የሆነ እንደሆነ ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፱· <u>ከባድ ሁኔታ</u>

ከላይ የተዘረዘሩት ወንጀሎች በተፈጸሙ ጊዜ በሕይወት፣ በአካል ወይም በጤና ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ እንደጥፋቱ ክብደት ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም ሞት ይሆናል።

፲· <u>የሥራ ግዴታን ስለመጣስ</u>

በበረራ ደህንነት ላይ ሊፈጸም የሚችለውን ማንኛውንም ወንጀል ለመከላከል ወይም ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት ሠራተኛ የሥራ ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ ቀርቶ በበረራ ላይ ወይም በአገልግሎት ላይ ባለ አይሮፕላን ወይም ለበረራ ደህንነት በሚያገለግሉ መሣሪያዎች ወይም ተቋሞች ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሣሪያ ወይም ዕቃ ተቀምጦ ቢገኝ ከ፭ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤ ድርጊቱ በሕይወት፣ በአካል ወይም በጤና ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ፳፭ ዓመት ጽኑ እስራት ሊደርስ ይችላል።

፲፩· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2) Whosoever intentionally destroys or damages air navigation facilities or equipment, or interferes with their operation, which act is likely to endanger the safety of an aircraft in flight, is punishable with rigorous imprisonment from fifteen to twenty-five years.

8. *Communication of False Information Endangering the Safety of an Aircraft in Flight*

1) Whosoever negligently communicates information which he knows to be false, thereby endangering the safety of an aircraft in flight, is punishable with rigorous imprisonment from five to fifteen years.

2) Whosoever intentionally communicates information which he knows to be false, thereby endangering the safety of an aircraft in flight, is punishable with rigorous imprisonment from fifteen to twenty-five years.

9. *Aggravating Circumstances*

Where the offences committed under the preceding Articles cause damage to life, person or health, the punishment is, having regard to the gravity of the offence, rigorous imprisonment for life or death.

10. *Breaches of Duty*

Whosoever, charged with the responsibility of preventing or controlling offences against the safety of aviation, allows the placing of a device or substance which causes damage to an aircraft in flight or in service or to air navigation equipment or facilities, by failing to properly discharge his duties, is punishable with rigorous imprisonment from five to fifteen years; in cases where the offence causes damage to life, person or health, the punishment is rigorous imprisonment not exceeding twenty-five years.

11. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 22nd day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of February, 1996

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA